# የዜጎች መድረክ

ኢዜማ

ቅፅ 1 ቁጥር 40 ሚያዝያ 24 ቀን 2012 ዓ.ም

በኢዜማ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ

## የኮሮና ቫይረስና ተጓዳኝ ጉዳዮች

ባንተይገኝ ታምራት (ዶ/ር)



# ‹‹ውይይቱ ትልቅ ፋይዳ አለው፤ በጠቅላይ ሚኒስትሩም ቀጣይነት እንደሚኖረው ቃል ተገብቶልናል››

የዜጎች መድረክ ሚያዝያ 24 ቀን 2012ዓ.ም



የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኀበራዊ ፍትሕ (ኢዜማ) በጠቅላይ ሚኒስትር ፅ/ቤት ሚያዝያ 21 ቀን 2012 ዓ.ም "ኮቪድ-19፣ ምርጫን ማራዘምና የሕግ አማራጮች" በሚል ርዕስ ከመንግሥትና ከሌሎች ተፎካካሪ ፓርቲዎች ጋር ውይይት ማካሄዱን የፓርቲው ሊቀመንበር የሺዋስ አሰፋ ለዜጎች መድረክ ገለፁ።

ሊቀመንበሩ፣ ውይይቱ ካለፉት ሁለት ውይይቶች ማለትም የምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ ስለ ኮሮና ወረርሽኝና ስለቀጣዩ ምርጫ ፓርቲዎችን ካወያዩበት እና ጠቅላይ ሚኒስትሩ ስለ ኮሮና ወረርሽኝና ስለ አስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ፓርቲዎችን ካወያዩበት የቀጠለ መሆኑን ጠቁመዋል። የፌደራል ጠቅላይ አቃቤ ህግ ምክትል አቃቤ ሕግ ጌዲዮን ጢሞቲዮስ (ዶ/ር) ለውይይቱ መነሻ ሃሳብ ማቅረባቸውንና ባቀረቡት የመነሻ ሀሳብ ላይም ምርጫውን ላላመካሄድ የተጋረጠው ሁኔታ፣ ያለው የህግ አማራጭ እና ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎች መዳሰሳቸውን አስረድተዋል። መፍትሔ ያሏቸውን አራት አማራጮች ም/አቃቤ ሕጉ አቅርበዋል።

እነዚህም:-የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤትን መበተን፤ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ማወጅ፤ ሕገ መንግስትን ማሻሻል፤ የሕገ መንግስት ትርጓሜ መጠየቅ የሚሉ ናቸው።

በኢዜማ በኩል የተያዘው አቋም ምን ነበር? በሚል ላነሳንላቸው ጥያቄ ሊቀመንበሩ ለውይይቱ በድንገት የተጠሩ በመሆኑ እንደ ኢዜማ ይሄን አቋም ነው ማራመድ ያለብን ብሎ አቋም ይዘው እንዳልሄዱ ተናግረዋል። ከቀረቡት አማራጮች ውስጥ ሕገ መንግስቱን ማሻሻል እና የሕገ መንግሥቱን ትርጓሜ መጠየቅ በጣምራ ቢታዩ የተሻለ እንደሆነ ሊቀመንበሩ ጠቁመዋል።

ውይይቱ ህጋዊና ፖለቲካዊ መፍትሄ ለማፈላለግ እጅግ አስፈላጊ ነው ያሉት አቶ የሺዋስ አሰፋ፣ ሕገመንግስቱ ይሄን አይነት አስቸጋሪ ሁኔታ የሚታለፍበት አንቀፅ የለውም፤ ስለዚህ ውይይቱ ትልቅ ፋይዳ አለው በጠቅላይ ሚኒስትሩም ቀጣይነት እንደሚኖረው ቃል ተገብቶልናል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ዘንድሮ ለማካሄድ ቀነ ቀጠሮ ቆርጦለት የነበረውን ምርጫ በጊዜው ማካሄድ አልችልም ብሎ ለሕዝብ እንደራሴዎች ምክር ቤት ሀሳብ አቅርቦ እንደነበር የሚታወስ ነው፡፡ የሕዝብ እንደራሴዎች ምክር ቤት፣ መጪውን ሐገራዊ ምርጫ በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ ማካሄድ ስለማይቻል፣ ምን ይደረግ የሚለውን የመጨረሻ የውሳኔ ሐሳብ ይዞ እንዲቀርብ ጉዳዩን ለሕግ፣ ፍትህ እና ዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ መርቶታል።

# ‹‹ደም መለገስ ሕይወት የማዳን ጉዳይ ነው፤ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ጤነኛ እስከሆነ ድረስ ማድረግ ያለበት ተግባር ነው››

የዜጎች መድረክ ሚያዝያ 24 ቀን 2012ዓ.ም



የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኀበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) በአዲስ አበባ ከተማ ምርጫ ወረዳ 16 አስተባባሪነት በተካሄደው የደም ልገሳ መርሀግብር ላይ ተሳታፊ የነበሩት አንማው አንተነህ (ዶ/ር) ‹‹ደም መለገስን ሁሉም ኢትዮጵያዊ ፖለቲሳይዝ ማድረግ ሳያስፈልገው ሰውን ለማዳን ብቻ የሚተገብረው ተግባር መሆን አለበት››ሲሉ ገለፁ፡፡

ዶክተሩ ‹‹ከረጅም ግዜ አመታት በፊት ደም ሰጥቼ አውቃለሁ ይሄ አራተኛ ግዜዬ ነው እስከ መቶም ሰባም ግዜ ድረስ የሚሰጡ ሰዎች አሉ፡፡ ጤነኛም ሆነው በአመት እስከ ሶስት ጊዜም አራት ጊዜም የሚሰጡ ሰዎች አሉ፡፡ ይሄ ህይወት የማዳን ጉዳይ ነው የፖለቲካ ጉዳይ አይደለም፤ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ጤነኛ እስከሆነ ድረስ ማድረግ ያለበት ተግባር ነው›› ብለዋል ፡፡

በተለይ አሁን ባለንበት ግዜ ከኮቪድ 19 ወረርሽኝ ጋር ጦርነት የገጠምንበት ጊዜ እንደመሆኑ ሰውን ለማዳን በተቻለን አቅም ደም መስጠት ይገባል ያሉት አንማው አንተነህ (ዶ/ር) ‹‹ደም በመስጠት ነፍስ እናድናለን፤ ኢትዮጵያውያንን እናድናለን ሲሉ የደም ልገሳውን ፋይዳ አስረድተዋል፡፡ ‹‹ይህ የምሰጠው ደም የሚያድነው ማንን እንደሆነ አላውቅም ሰው ነው ግን የሚያድነው፤ የሚጠላኝም ሆነ የሚወደኝ ሰው ሊሆን ይችላል ነገር ግን ሰው እስካዳነ ድረስ ልገሳው አስፈላጊ ነው፡፡ ማንም ሰው ደም መለገስን ፖለቲካ አድርጎ ሳይመለከተው በዚህ ሰብአዊ ተግባር ላይ ቢሳተፍ መልካም ነው›› ሲሉ ልገሳውን ከፖለቲካ ጋር ሳያገናኙ ከሰብአዊ ተግባር ጋር ብቻ በማያያዝ ዜጎች በደም ልገሳ ተግባር ላይ መሰማራት እንዳለባቸው ተናግረዋል፡፡


## አድራሻ

ስልክ
+251118592950

ኢሜይል
ethzema@gmail.com

ትዊተር
www.twitter.com/ethzema

ፌስቡክ
www.facebook.com/ethzema

የኢትዮጵያ ዜጎች
ለማኀበራዊ ፍትህ
(ኢዜማ)

ሚያዝያ 24 ቀን 2012 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# የኮሮና ቫይረስና ተጓዳኝ ጉዳዮች

ባንተይገኝ ታምራት (ዶ/ር) በእንስሳት ህክምና ዘርፍ የመጀመሪያ ዲግሪ እንዲሁም በትሮፒካል አኒማል ፓቶሎጂ ሁለተኛ ዲግሪ አላቸው፡፡ የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትሕ (ኢዜማ) የመንግስት ትይዩ ካቢኔ እጩ ተወካይ ናቸው፡፡ «የኮሮና ቫይረስና ተጓዳኝ ጉዳዮች» በሚል ርዕስ ስለ ኮሮና ቫይረስ አመጣጥና ኮሮናን እና ሌሎች ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎችን ለመቆጣጠር በሚደረገው እንቅስቃሴ ውስጥ ከመንግስትና ከህብረተሰቡ ምን ይጠበቃል በሚል ሙያዊ ማብራሪያ ያቀረቡበትን ተከታዩ ፅሁፋቸውን ይዘን ቀርበናል፡፡ መልካም ንባብ!



የሰው ልጅ ከጥንት ጀምሮ እንስሳትን ለምግብነትና ለንግድ ስራ ሲል የማደን ልምድ ይከተል እንደነበረ ከተለያዩ የታሪክ መዛግብት መረዳት ይቻላል፡፡ በእነዚህ እንቅስቃሴዎች ውስጥም በንክኪም ይሁን የነዚህን እንስሳት ስጋና የስጋ ውጤቶች በመመገብ አያሌ ሊባሉ የሚችሉ የእንስሳት በሽታዎች ከእንስሳት ወደ ሰው በቀላሉ በመተላለፍ ክቡር የሆነውን የሰው ልጅ ሕይወት ሲቀጥፉ መቆየታቸው ይታወቃል፡፡ ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታወች በቫይረስ፣ በባክቴሪያ፣ በፈንገስ እንደዚሁም በፓራሳይት አማካኝነት ሊፈጠሩ የሚችሉ ሲሆን በተለይም በቫይረስ አማካኝነት የሚከሰቱ የበሽታ አይነቶች ካላቸው የተለዋዋጭነት ባህሪ እንደዚሁም በሰውም ሆነ በእንስሳት ላይ ከሚያደርሱት ጉዳት አኳያ ሲመዘኑ ትልቁን ድርሻ ይይዛሉ፡፡ በእኛ እድሜ ከእንስሳት ወደ ሰው የተላለፉትን የወረርሽኝ አይነቶችን እንኳን ብንቃኝ ብዙ የአፍሪካ ሃገራትን እያስጨነቀ ያለው ኢቦላ ከሌሊት ወፎች፣ ኤች አይቪ ከዝንጀሮ እንደዚሁም የእብድ ውሻ በሽታ ከስሙ መረዳት እንደሚቻለው ከውሻ የመጡ ስለመሆናቸው መረዳት ይቻላል፡፡ የዚህ ፅሁፍ ዋና ዓላማ አለማችንን ብሎም ሃገራችንን እያስጨነቀ ስላለው ኮቪድ--19 መጠነኛ የሆነ ጭብጥ ለማስጨበጥ ሲሆን ለአረዳድ ይመች ዘንድ በሚከተለው መንገድ ለመቃኘት ተሞክሯል፡፡

1. ቫይረስ ምንድን ነው ?
2. የመተላለፊያ መንገዶችስ?
3. የኮረና ቫይረስ ታሪካዊ ክስተት
4. የመከላከያ ዘዴዎች
5. የሚያስከትለው ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ተጽዕኖ
6. ኮረናን እና ሌሎች ከእንሰሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎችን ለመቆጣጠር በሚደረገው እንቅስቃሴ ውስጥ ከመንግስትና ከህብረተሰቡ ምን ይጠበቃል?

## ቫይረስ ምንድን ነው?

ቫይረስ ማለት በዓይን የማይታይ በማጉሊያ መሳሪያዎች(ማይክሮስኮፕ) ዕገዛ ብቻ የሚታይ በሽታ አምጪ ተህዋስ ሲሆን እንሰሳትን፣ ሰውን እንደዚሁም እጽዋትን ያጠቃሉ፡፡ እነዚህ ቫይረሶች በአይነት,፣ በመጠን እንደዚሁም በቅርጻቸው የሚለያዩ ሲሆን አንዳንዶቹ እንሰሳትን ሌሎች ደግሞ ሰውን ብቻ በተናጠል የሚያጠቁትን ያህል የተወሰኑ ቫይረሶች ሰውንም ሆነ እንሰሳትን በማንኛውም ጊዜ ሊጎዱ እንደሚችሉ ይታወቃል፡፡ ሁሉም የቫይረስ አይነቶች በባህሪያቸው በሰውም ሆነ በእንስሳት ሴል ውስጥ ከገቡ በኋላ በአጭር ጊዜያት ውስጥ በሺዎች በመባዛት ጉዳት እንደሚያደርሱ መገንዘቡ ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡

የመተላለፊያ መንገዶችስ ምን ምን ናቸው?

የቫይረሶች የመተላለፊያ መንገዶች እንደ የቫይረሱ ልዩ ባህሪያት የሚለያይ ነው፡፡ አንዳንዶቹን ለመጥቀስ ያህል፡-

- በምግብ፣ በውሃ እና በንክኪ ከሚተላለፉት ውስጥ የአንጀትና የጨጓራ ቫይረሶች(Rota virus)
- በደም መጣጭ ኢንሴክቶች አማካኝነት
- በሳልና በማስነጠስ ከሚተላለፉት ውስጥ (Influenza virus, covid--19)
- እንደ HIV አይነት ቫይረሶች በግብረ ስጋ ግንኙነትና በተበከለ ደም አማካኝነት ይተላለፋሉ
- የታመሙ እንሰሳትን በመተሻሸት
- ጥሬ ስጋ ወይም በደንብ ያልበሰለ ስጋ በመብላት እንደዚሁም በደንብ ያልፈላ ወተት በመጠጣት
- ከአፍና ከአፍንጫ በሚወጡ ጥቃቅን እንክብሎች
- ከዱር አራዊት ወደ ተለያዩ የቤት እንስሳት ብሎም ወደ ሰው የሚተላለፉ ይገኙበታል፡፡ ▶



## ▶ የኮረና ቫይረስ ታሪካዊ ክስተት

ብዙዎች እንደሚገምቱት የኮሮና ቫይረስ በሽታ አሁን በዚህ ዘመን የተፈጠረ እና የተለየ ሳይሆን ከዚህ በፊትም የነበረ መሆኑን አንዳንድ ጥናቶች ያመላክታሉ፡፡ በተለይም ቫይረሱ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ከ1960 ዓ/ም ጀምሮ ይታወቅ እንደነበረ ሆኖም ግን በወቅቱ በሽታው ያጠቃ የነበረው እንስሳትን ብቻ እንደነበር መገንዘብ ይቻላል፡፡ የኮሮና ቫይረስ የእንስሳትን የመተንፈሻ አካል የመጉዳቱን ያህል አንዳንድ እንስሳት ምንም አይነት የበሽታ ምልክት እንደማያሳዩና በተጻራሪው ሌሎች እንስሳት በሽታውን መቋቋም ባለመቻላቸው ለሞት ይዳረጉ እንደነበር ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ቫይረሱን በተመለከተ የተለያዩ የዓለም ተመራማሪዎች ባደረጉት ጥናት መሰረት ወደ 7 የሚደርሱ ሰዎችን የሚያጠቁ የኮሮና ቫይረስ ዝርያዎች መኖራቸውን በጥናት ተረጋግጧል፡፡ ከነዚህም ውስጥ

አንዱ MERS—COV (meddle East Respiratory syndrome) ሲሆን በሰው ልጆች የመተንፈሻ አካላት ላይ ከፍተኛ ሊባል የሚችል ጉዳት ሲያደርስ እንደነበረ ታውቋል፡፡ በሽታው ለመጀመሪያ ጊዜ በ2012 ዓ/ም ሳውዲ አረቢያ ውስጥ ከግመሎች (Dromedarios) ወደ ሰዎች በንክኪ የተላለፈ ሲሆን በወቅቱ ወደ 80% የሚደርሱ ሰዎች በበሽታው ተይዘው እንደነበር እና ከተያዙት ሰዎች ውስጥ 35% የሚደርሱት ሕይወታቸው እንዳለፈ እና በዚህ ወቅት በሽታው በአንዳንድ ታዳጊ በሆኑ ሃገራት ካልሆነ በስተቀር በቀሪው ዓለም የተወገደ መሆኑንን መገመት ይቻላል፡፡

ሁለተኛው የኮረና ቫይረስ ዝርያ Corona Virus SARS (sever acquit respiratory syndrome) ሲሆን ይሄም እንደ መጀመሪያው ቫይረስ ሁሉ በሰዎች የመተንፈሻ አካል ላይ ጉዳት የሚያደርስ ሲሆን የመጀመሪያ የቫይረሱ ተጠቂዎች በ2002ዓ/ም ቻይና ሃገር እንደተገኙ ከዚያም ወደ ተለያዩ ሃገራት እንደተዛመተ ይታወቃል በሽታውም ከጥርኝ (civeta) ከተባለ እንስሳ ወደ ሰው የተላለፈ እንደነበር መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ምንም እንኳን በበሽታው ምክንያት ወደ 8000 የሚደርሱ ሰዎች ተጠቅተው የነበረ ቢሆንም ከ 2003ዓ/ም ጀምሮ የዓለም የጤና ድርጅት በሽታው በቁጥጥር ስር የዋለ መሆኑንን ማረጋገጫ ሰጥቷል፡፡

ሶስተኛው Viurs Corona Viurs SARS-cov-2 Wuhan በተባለች የቻይና ከተማ በ 2019 የተከሰተ ሲሆን አንዳንድ የከተማዋ ነዋሪዎች በሳንባቸው ላይ የተለያዩ ችግሮች ይታዩባቸው እንደነበርና ጉዳዩን ተከትሎ የቻይና ሃኪሞች በወቅቱ ይህንን በሽታ ከመጀመሪያው በ2002 ተከስቶ ከነበረው የ CoronaVirus ለይቶ ለማወቅ በጣም ተቸግረው እንደነበር ጥናቱ ያትታል፡፡ በተጨማሪም በ 3 ወር ጊዜ ውስጥ ከ 200,000 ሰዎችን ከማጥቃቱ ባሻገር ወደ 100 የዓለም ሃገራት በቀላሉ ለመዛመት ችሏል፡፡ የዚህ በሽታ የመጀመሪያዋ ተጠቂ የሌሊት ወፍ ስትሆን በሽታውን ወደ ፓንጎሊን ወደ ተባለ አጥቢ እንሰሳ በማስተላለፍ ይሄ እንስሳም በተዋረድ በሽታውን ወደ ሰው እንዳስተላለፈው ይገመታል፡፡

ሃገራችንን ጨምሮ ዓለምን ከዳር እስከዳር እያስጨነቀ ያለው የ Covid-19 ወረርሽኝ እንደሌሎች የ Corona አይነቶች ሁሉ «Wuhan» ከተማ ከሚገኝ ልቅ የእንስሳት ገበያ ሲሆን በዚህ የገበያ ማዕከል የተለያዩ የአእዋፍ አይነቶች፣ የቁም እንስሳት፣ ስጋና የስጋ ውጤቶች እንደዚሁም የተለያዩ የዱር አራዊቶች ግብይት የሚደረግበት ቦታ መሆኑ ይታወቃል፡፡ የመጀመሪያው ታማሚ በ2019 ከተለየ በኋላ እሱን ተከትሎ 41 የሳንባ ችግር ያለባቸውን ሰዎች በልዩ ስፍራ ኳራንታይን ውስጥ በማስገባት በተደረገ ምርመራ Covid-19 ያለባቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ከነዚህ ውስጥ 1/3 ኛው ወይም 66% የዱር እንሰሳት ከሚሸጡበት እዚሁ የገበያ ማዕከል ጋር ሰፊ ግንኙነት የነበራቸው መሆኑ ታውቋል፡፡ ይህንንም መነሻ በማድረግ የቻይና መንግስት የበሽታው ዋና ምንጭ ልቅ በሆነና ጥንቃቄ በጎደለው መልክ የሚከናወነው የእንስሳት ግብይት መሆኑን በመገንዘብ የገበያ ማዕከሉ ሙሉ በሙሉ እንዲዘጋ አድርጓል፡፡ ይህም እርምጃ በሽታውን ለመቆጣጠር የሚደረገውን ጥረት አግዟል ብሎ ለመውሰድ ይቻላል ፡፡

የCovid-19 ወረርሽኝን በተመለከተ ከላይ እንዳየነው ሁሉ ከሌሊት ወፍ ወደ ፓንጎሊን ከፓንጎሊን ወደ ሰው እንደተላለፈ አመላካች ጥናቶች እንደተጠበቁ ሆነው ኒው ዮርክ ግዛት ውስጥ በተደረገ ተጨማሪ ጥናት የፓንጎሊኒ ስጋ የበሉ ነብሮች በቫይረሱ መያዛቸውን ለማረጋገጥ ችለዋል፡፡ ባጠቃላይ ይህ ፓንጎሊን የተባለ አጥቢ እንስሳት በብዙ ሃገራት ለምግብነት እንደዚሁም የላይኛው የሰውነት ክፍሉ ለተለያዩ መድሃኒቶች መቀመሚያ እንደሚያገለግለው ሁሉ ለዚህ በሽታ ስርጭትም አሉታዊ ሚናው ቀላል አለመሆኑን ለመረዳት ይቻላል፡፡

## የኮሮና ቫይረስ የመከላከያ ዘዴዎች

የኮሮና ቫይረስን የስርጭት ፍጥነት እንደዚሁም የሚያደርሰውን ጉዳት ከልብ የተረዱ የዓለም ጠበብት የመከላከያ ክትባትም ሆነ መድሃኒት ለማግኘትና የዓለምን ህዝብ ከሰቆቃ ለማውጣት ቀን ከሌሊት እየሰሩ ቢሆንም መፍትሄውን እንዲህ በቀላሉ ማምጣት ግን እጅግ ፈታኝ ሆኖባቸዋል፡፡

በዚሁም ምክንያት አያሌ በሚሊየን የሚቆጠሩ የዓለም ህዝቦች በበሽታው ሰለባ እንደሆኑና በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ደግሞ ክቡር ሕይወታቸውን አትጠዋል፡፡ ባጠቃላይ ለቫይረሱ ተመጣጣኝ የሆነ ወይም ፈዋሽ መድሃኒትም ሆነ የመከላከያ ክትባት በሙከራ ላይ መሆኑን በመረዳት በሽታውን ለመከላከል ያለን ብቸኛ አማራጭ በዓለም ጤና ድርጅት የወጡትን የቅድሚያ ጥንቃቄ እርምጃዎችን ተግባራዊ ማድረግ ሲሆን እንደሃገርም አሁን ወረርሽኙን ተከትሎ በህብረተሰቡ ዘንድ የሚታዩት መዘናጋቶች በብዙ የዓለም ሃገራት እንዳየነው ሁሉ ዋጋ እንዳያስከፍሉን በቂ ሊባል የሚችል ዝግጅትና ጥንቃቄ ማድረግ እንደተጠበቀ ሆኖ የጤና ባለሙያዎች የሚሰጡትን ሙያዊ ምክርም በበጎነት በመመልከት ወደ ተግባር ልንቀይረው ይገባል፡፡

የኮረና ቫይረስ የሚያስከትላቸው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ተጽዕኖ

ሃገራችን ኢትዮጵያ የብዙ የተፈጥሮ ሃብት ባለቤት መሆኗ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ ከረጅም ዓመታት ጀምሮ ከውጭና ከውስጥ በሚደርስባት ጫና ምክንያት ሃብቷን አሟጣ በመጠቀም የዜጎቿን መሰረታዊ ፍለጎት ማሟላት አልቻለችም፡፡ በዚህም ምክንያት ልጆቿ ለእንጀራ ፍለጋ የስደትን ጉዞ በመምረጥ ከሚወዷት ሃገራቸውና ወገናቸው ተነጥለው ኑሮን በባዕድ ሃገራት በመግፋት ላይ ይገኛሉ፡፡ ኢኮኖሚያችንም በአብላጫው የተመሰረተው በግብርና ዘርፉ ላይ ሲሆን የግብርና ዘርፍ በተለያዩ ቴክኖሎጂዎች የማይታገዝና ኋላ ቀር የሆኑ የአስተራረስ ዘዴዎችን የሚከተል በመሆኑ ምክንያት አይደለም የውጭ ምንዛሬ በማምጣት የሃገሪቱን ኢኮኖሚ ማነቃቃት ይቅርና የህዝቡን የምግብ ፍላጎት እንኳ ማሟላት ባለመቻሉ ምክንያት ቁጥሩ ቀላል የማይባል ህዝብ የሴፍቲኔት ተረጅ ሆኗል፡፡ በዚህ ብቻም አያቆምም፡፡ እድሜያቸው ለስራ የደረሱ ብዙ ወጣቶች ዛሬም ስራ አጥናቸው፡፡ ባጠቃላይ ኢኮኖሚያችን በውጭ ሃገራት ብድርና እርዳታ ላይ የተንጠለጠለ በመሆኑ ተከታታይነትም ሆነ አስተማማኝነቱ ▶

▶ አጠያያቂ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ይህ በእንዲህ እያለ ከድጡ ወደማጡ እንዲሉ በነበረን የኢኮኖሚ ቸግር ላይ የኮሮና ወረርሽኝ ተጨምሮበት ቀጣይ እጣ ፋንታችን ምን ሊሆን እንደሚችል መገመቱ አያዳግትም፡፡ ዛሬ አይደለም ስራ የሌላቸውን ወጣቶች ስራ ለመስጠት ይቅርና ስራ የነበራቸው ድርጅቶች ሳይቀሩ ስራ አቁመዋል፡፡ ይህ ማለት እንግዲህ በስራቸው የነበሩ ሰራተኞችም ይበተናሉ ማለት ነው፡፡ ከዚህ አኳያ የቫይረሱ ስርጭት አድማሱን እንዳያሰፋ ያለን መልካም ምኞት እንደተጠበቀ ሆኖ ችግሩ ለተጨማሪ ወራት እየተስፋፋ የሚሄድ ከሆነ በሃገራችን የሚፈጠረው የኢኮኖሚ ችግር ውሎ አድሮ ማህበራዊ ቀውስ የመውለዱ ጉዳይ አይቀሬ ከመሆኑ ባሻገር ሃገሪቱን ወደ ስርዓት አልበኝነት በመውሰድ የጸጥታ ችግር እንዳይፈጠር ሁላችንም ትኩረት ሰጥተን መንቀሳቀስ ይገባናል፡፡

የኮረና ቫይረስ እና ሌሎች ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎችን (Zoonotic Disease) ለመከላከል ከህብረተሰቡና ከመንግስት ምን ይጠበቃል?

ለወደፊቱም ቢሆን በዓለም ልክ እንደኮረና ሁሉ ከእንስሳት ወደ ሰው በቀላሉ ሊተላለፉ የሚችሉ ሌሎች ወረርሽኞች የመከሰታቸው ጉዳይ አይቀሬ በመሆኑ የየትኛውም ሃገር መንግስትና ህዝብ እራሱን ሁሌ ዝግጁ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ ብዙውን ጊዜ እንደዚህ አይነት ወረርሽኞች በሚከሰቱበት ወቅት የተለያዩ ሃገር መንግስታት ወረርሽኙን ለመመከት የተለያዩ ህጎችን ያወጣሉ፡፡ በእኛም ሃገር በቅርቡ የወጣውን የአስቸኳይ የጊዜ አዋጅ ማየት ይቻላል፡፡ ነገር ግን እንደዚህ ዓይነት ህጎች በ 3 ምክንያቶች ሙሉ በሙሉ ሲተገበሩ አይታዩም፡፡ እነሱም፡-

1ኛ. በሁሉም የዓለም ሃገራት የህዝብ ቁጥር ከዕለት ወደ ዕለት እየጨመረ መምጣት መመሪያውን ተግባራዊ ለማድረግ አዳጋች መሆኑ፤

2ኛ. በማህበረሰቡ ውስጥ ያለው የባህል ስብጥርና የባህል ተጽዕኖ፤

3ኛ. የሚወጡትን መመሪያዎች አስፈጻሚው አካል ታች ድረስ ወርዶ ለማስፈጸም አለመቻል ይገኙበታል፡፡

## ከህብረተሰቡ የሚጠበቁ ዋና ዋና ጉዳዮች

- ኮረናን ጨምሮ ሌሎች ተላላፊ በሽታዎች ከእንሰሳት ወደ ሰው ስለሚተላለፉ ከቤትም ይሁን ከዱር እንስሳት ጋር የምናደርገውን አካላዊ ንክኪ ማስወገድ፤
- የቤት እንስሶች ካሉን ህመም ሲሰማቸው ወደ እንሰሳት ህክምና ማዕከላት ወስዶ የማሳከም እና በወቅቱ የማስከተብ ልምድ ማዳበር፤
- ጥሬና በደንብ ያልበሰሉ ስጋና የስጋ ውጤቶችን እደዚሁም ያልተፈላ ወተት ከመመገብ ሙሉ በሙሉ መቆጠብ፤
- እንስሳትን ለምግብነት ከገበያ በምንገዛበት ወቅት ቢያንስ የምንገዛው እንስሳ የፈዘዘ፣ የተቅማጥ ምልክት፣ የሳል ምልክት፣ እንደዚሁም በአፍና በአፍንጫ ያልተለመዱ ፈሳሾች የሌሉበት መሆኑን ማረጋገጥ ይገባል፤
- ምንም እንኳን በሁሉም የሃገራችን ክፍሎች የእንሰሳት ዕርድ ቦታ (Abattoir) አለ ባይባልም ባሉትም ቢሆን እንሰሳትን ወስደን የማሳረድ ልምድ ልናዳብር ይገባል፡፡ በቤታችን የምናሳርድም ከሆነ አራጁና እረዳቱ እንደሳልና ተቅማጥ የመሳሰሉ የበሽታ ምልክቶች የሌሉባቸው መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፤
- በበሽታም ሆነ በድንገት የሞተን እንስሳ ቆዳ መግፈፍም ሆነ ስጋውን ለምግብነት ለመዋል መሞከር አደጋው እጅግ የከፋ ስለሆነ ብዙ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ እንደዚህ አይነት አጋጣሚዎች ሲከሰቱ እንስሳውን ጥንቃቄ በተሞላበት አኳሃን መቅበር ወይም ማቃጠል ያስፈልጋል፡፡

## ከመንግስት ምን ይጠበቃል?

- ኢትዮጵያ የዓለም የእንስሳት ጤና ድርጅት (OIE) እና የዓለም ንግድ ድርጅት(WTO) አባል ሃገር እንደመሆኗ መጠን በሌሎች ሃገራት የተወገዱ ነገር ግን በእኛ ሃገር ያልተወገዱ ከእንስሳት ወደ ሰው(Zoonotic disease) የሚተላለፉ በሽታዎችን ለማስወገድ የተጠናቀረ ስራ መስራት፤
- ኮሮናን ጨምሮ ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ የበሽታ አይነቶችን በዘላቂነት ለማስወገድ ይቻል ዘንድ የሃገሪቱን የእንስሳት ጤና ጥበቃ ዘርፍ በቁሳቁስና በቴክኖሎጂ እንደዚሁም በበቂ የተማረ የሰው ሃይል እንዲታገዝ ማድረግ፤
- የእንስሳትን ጤና መጠበቅ የህብረተሰብን ጤና መጠበቅ መሆኑን በመረዳት እንደ ማህበረሰብ ጤና ኢንስቲትዩት፤ የጤና ሚኒስተርና የእንሰሳት ጤና ጥበቃው ዘርፍ ተናበው ሊሰሩ የሚችሉበት የአሰራር ስርዓት መዘርጋት፤
- አሁን ያለውን ልቅ የሆነ የእንስሳት ግብይት ስርዓት በማስያዝ የእንስሳት ግብይቶች በተዘጋጁ የገበያ ማዕከላት ብቻ እንዲከናወኑ በማድረግ የተለያዩ በሽታዎችን መቆጣጠር የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት፤
- ህብረተሰቡ እንስሳትን ወደ ቄራዎች ወስዶ በማሳረድ በሽታን ለመከላከል የሚደረገውን ጥረት ማገዝ እንዲችል ተከታታይ የሆኑ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች በሚመለከታቸው የዘርፉ ባለሙያዎች እንዲሰጡ ማድረግ፤
- አሁን የተከሰተውን የኮሮና ወረርሽኝ ተከትሎ አንዳንድ በግል እየተመረቱ የሚወጡ ሳኒታይዘር እንደዚሁም የፊትና የአፍንጫ መሸፈኛዎች በደረጃ መዳቢዎች ያልታዩና እንደማንኛውም ሸቀጥ በየመነሃሪያዎችና ብዙ ህዝብ በሚበዛባቸው አካባቢዎች ጥንቃቄ በጎደለው መልኩ መሸጡ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ስለሚያመዝን ገደብ ቢበጅለት፡፡

በብዙ የዓለም ሃገራት ለምግብነት እና ለመድሃኒት ቅመማ እንደዚሁም ለኮሮና ክስተት መነሻ ይሆናል ተብሎ ግምት የተሰጠው ፓንጎሊን (pangolin) ይህንን ይመስላል



ማሳሰቢያ ፡-አሁን ባለው የኮረና ቫይረስ ስርጭትና የመተላለፊያ መንገዶች ከእንስሳት ወደ ሰው ይተላለፋል ብሎ ለማስቀመጥና ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የበለጠ የሪሰርች ጥናት ውጤቶችን መጠበቅ እንደሚገባ ግንዛቤ ይወሰድ ዘንድ እናሳስባለን፡፡



# በአዲስ አበባ ከተማ አራት የምርጫ ወረዳዎች ደም ለገሱ

የዜጎች መድረክ ሚያዝያ 24 ቀን 2012ዓ.ም







የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) የኮቪድ-19 ወረርሽኝን ለመቆጣጠር እና ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት ለመቀነስ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚደረገውን ርብርብ ለማገዝ የፓርቲው ብሔራዊ ሥራ አስፈጻሚ መመሪያ በማፅደቅ የፀረ-ኮቪድ-19 ግብረ ኃይል ያቋቋመ ሲሆን፣ ግብረ ሀይሉ የኮቪድ 19 ወረርሺኝን ከመቆጣጠርና ከመከላከል ስራ በተጓዳኝ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተከሰተውን የደም እጥረት ችግር ለመቅረፍ ለአንድ ሳምንት የሚቆይ የደም ልገሳ መርሀ ግብርን ይፋ ማድረጉን ተከትሎ በአዲስ አበባ ከተማ የምርጫ ወረዳ 16፣ 20-21፣ 22 እና 24 አባላት ሚያዚያ 23 ቀን 2012 ዓ.ም በኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ዋና ጽ/ቤት በመገኘት ደም ለገሱ ፡፡

«በደም እጥረት ምክንያት ዜጎች ለህልፈት መዳረግ የለባቸውም» በሚል መሪ ቃል ግብረ ሀይሉ፣ በሀገር አቀፍ ደረጃ ላጋጠመው የደም እጥረት ለመቅረፍ ትኩረት አድርጎ በመስራት በመላ ሀገሪቱ የሚገኙ የፓርቲው አደረጃጀት መዋቅሮች በደም ልገሳው መርሀግብር ላይ ተሳታፊ እንዲሆኑ ጥሪውን ያቀረበ ሲሆን፤ መርሀግብሩ ይፋ ሲደረግ የፓርቲው ከፍተኛ አመራሮች በብሄራዊ የደም ባንክ ዋና መምሪያ በመገኘት የደም ልገሳ ማድረጋቸው ይታወሳል፡፡ ይህንን ተከትሎም በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገራት የሚገኙ የኢዜማ አባላት አዎንታዊ ምላሽ በመስጠት በደም ልገሳ መርሀግብሩ ላይ ተሳታፊ በመሆን ላይ ይገኛሉ፡፡

ይህ የደም መለገስ መርሀግብር የሚቀጥል ሲሆን የፊታችን ቅዳሜ ሚያዝያ 24 ቀን 2012 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ የምርጫ የወረዳ 19 አባላትና አመራሮች የደም ልገሳ እንደሚያደርጉ ካገኘነው መረጃ ለመረዳት ችለናል፡፡